የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ - ግንባት ፲ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 36
ADDIS ABABA-18th May 2007

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፭/፲፱፻፺፱
ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቅ መሬት ላይ ለሠፈረ ንብረት ስለሚከፈል ካሣ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ
........................................................................ገጽ ፫ሺ፮፻፳፪

## CONTENTS

Council Of Ministers Regulation No 135/2007
Payment of Compensation for Property Situated on landholding expropriated for public purposes Council of Ministers Regulations .................................... Page 3622

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፭/፲፱፻፺፱**
**ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቅ መሬት ላይ ለሠፈረ ንብረት ስለሚከፈል ካሣ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፭/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፲፬(፩) መሠረት ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቅ መሬት ላይ ለሰፈረ ንብረት የሚከፈል ካሳ ከንብረቱ ዋጋ በተጨማሪ ተነሺውን መልሶ ሊያቋቁም የሚያስችል የመፈናቀያ ካሳ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለመደንገግ ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቅ መሬት ላይ ለሰፈረ ንብረት ስለሚከፈል ካሣ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፭/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

*Council of Ministers Regulations No. 135./2007*
*COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS ON THE PAYMENT OF COMPENSATION FOR PROPERTY SITUATED ON LANDHOLDINGS EXPROPRIATED FOR PUBLIC PURPOSES*

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 14(1) of the Expropriation of Landholdings for Public Purposes and Payment of Compensation Proclamation No. 455/2005 with a purpose of not only paying compensation but also to assist displaced persons to restore their livelihood.

### *PART ONE*
### *GENERAL*

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Payment of Compensation for Property Situated on Landholdings Expropriated for Public Purposes Council of Ministers Regulations No. 135/2007"

2. *Definitions*

In these Regulations unless the context requires otherwise:

ያንዱ ዋጋ 3.40
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፩. "አዋጅ" ማለት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፭/፲፱፻፺፯ ነው፤

፪. "ኮሚቴ" ማለት በአዋጁ መሠረት የሚቋቋም የን ብረት ገማች ኮሚቴ ነው፤

፫. "ሰብል" ማለት በአንድ የአዝመራ ወቅት የሚዘራ ወይም የሚተከልና የሚሰበሰብ ማንኛውም ዕጽ ዋት ነው፡፡

፬. "የደረሰ ሰብል" ማለት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቅ መሬት ላይ ተዘርቶ ወይም ተተክሎ የሚገኝና በአዋጁ አንቀጽ ፬ መሠረት በሚሰ ጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ሊሰበሰብ የሚችል ሰብል ነው፤

፭. "ቋሚ ተክል" ማለት ለአመታት በየጊዜው ምርት የሚሰጥ ተክል ነው፤

፮. "ቤት" ማለት በከተማ ወይም በገጠር ለመ ኖሪያ፣ ለማምረቻ፣ ለንግድ፣ ለማህበራዊ ወይም ለሌላ አገልግሎት የተሠራ ወይም በመሠራት ላይ ያለ ማንኛውም ግንባታ ነው፤

፯. "ቀመር" ማለት በአዋጁ መሠረት በሚለቀቅ መሬት ላይ ለሠፈረ ንብረት በዚህ ደንብ መሠረት የሚከፈል ካሣ የሚሠላበት ዘዴ ነው፤

፰. "ክልል"፣ "ካሣ"፣ "የህዝብ ጥቅም"፣ "የአ ገልግሎት መስመር" እና "አስፈጻሚ መሥሪያ" ቤት የሚሉት በአዋጁ የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፤

፱. ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰ ውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለካሣ አተማመን

### ፫. የቤት ካሣ አተማመን

፩. የቤት ካሣ የሚሰላው ተመጣጣኝ ደረጃ ያለውን ቤት ለመስራት የሚያስፈልገውን የወቅቱን የካሬ ሜትር ወይም የነጠላ ዋጋ በማውጣት ይሆናል፡፡

፪. የቤት ካሣ ተመን

ሀ) ከቤቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የግቢ ንጣፍ፣ ሴፕቲክ ታንክና ሌሎች ስትራክቸ ሮች ለመሥራት የሚያስፈልገውን የወቅ ቱን ዋጋ፣ እና

1) "Proclamation" means the Expropriation of Landholdings for Public Purposes and Payment of Compensation Proclamation No. 455/2005;

2) "committee" means a property valuation committee established pursuant to the Proclamation;

3) "crops" means any plant sown or planted and harvested in one season;

4) "ripe crops" means plant sown or planted on a land holding to be expropriated for public purpose and that could be harvested within the notice period given under Article 4 of the Proclamation;

5) "perennial crops" means species of crops harvested regularly for years;

6) "building" means any structure constructed or under construction in an urban center or a rural area for residential, manufacturing, commercial, social or any other service;

7) "formula" means the methodology used for valuating compensation in accordance with these Regulations for Properties Situated on Landholdings Expropriated in Accordance with the Proclamation;

8) the terms "region", "compensation", "public purpose", "utility lines" and "implementing agency" shall have the meanings given to them under the Proclamation;

9) "person" means any natural or juridical person.

## PART TWO

## *ASSESSMENT OF COMPENSATION*

### 3. *Compensation for Buildings*

1. The amount of compensation for a building shall be determined on the basis of the current cost per square meter or unit for constructing a comparable building.

2. the compensation for a building shall include:

(a) the current cost for constructing floor tiles of the compound, septic tank and other structures attached to the building; and

ለ) ቤቱ በመነሳቱ ምክንያት የተገነቡ የአገል ግሎት መስመሮችን ለማፍረስ፣ ለማንሳት መልሶ ለመገንባት፣ ለመትከልና ለማገና ኘት የሚያስፈልጉትን ወጭዎች ግምት ይጨም ራል፣

፫. ቤቱ የሚፈርሰው በከፊል ሲሆን የቤቱ ባለቤት ቦታውን ለመልቀቅ ከመረጠ ለቤቱ ካሣ የማግ ኘት መብት አለው።

፬. ቤቱ የሚፈርሰው በከፊል ሲሆንና የቤቱ ባለቤት በቀሪው ቦታ ላይ ለመቆየት ከመረጠ ለፈረሰው የቤት አካል ብቻ ተሰልቶ ካሣ ይከፈለዋል። ሆኖም የቤቱ ባለቤት በቀሪው የቤቱ አካል የመቆየት ምርጫ አግባብ ባለው የከተማው ፕላን ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት።

፬. የአጥር ካሣ አተማመን

የአጥር ካሣ የሚሰላው ከሚፈርሰው አጥር ጋር በዓይነቱ ተመጣጣኝ የሆነ አጥር ለመስራት የሚያስፈልገውን የወቅቱን የካሬ ሜትር ወይም የነጠላ ዋጋ በማውጣት ይሆናል።

፭. የሰብል ካሣ አተማመን

፩. የሰብል ካሣ የሚሰላው ሰብሉ ለመሰብሰብ ደርሶ ቢሆን ኖሮ ሊሰጥ የሚችለውን ምርት መጠንና ምርቱ ሊያወጣ ይችል የነበረውን የአካባቢውን የወቅቱ የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

፪. ሰብሉ ለመሰብሰብ የደረሰ ከሆነ ባለንብረቱ በካሣ ክፍያ ፋንታ በአዋጁ አንቀጽ ፬ መሠረት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሰብሉን ሰብስቦ መውሰድ ይችላል።

፮. የቋሚ ተክል ካሣ አተማመን

፩. የቋሚ ተክል ካሣ የሚሠላው ተክሉ ፍሬ መስጠት ያልጀመረ ሲሆን ተክሉ በሚገኝበት ደረጃ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ወጭ ግምት በማስላት ይሆናል።

፪. ቋሚ ተክሉ ፍሬ ለመስጠት የጀመረ ከሆነ ካሣው የሚሰላው ተክሉ በአንድ ዓመት የሚያስገኘውን ምርት በወቅቱ የአካባቢው የገበያ ዋጋ በማባዛት እንዲሁም የመሬት ቋሚ ማሻሻያ ወጪን በመደመር ይሆናል።

(b) the estimated cost for demolishing, lifting, reconstructing, installing and connecting utility lines of the building.

3) The owner of a building shall have the right to claim compensation for the entire building by surrounding the total land in his possession where part of the building is ordered to be removed.

4) Compensation shall be paid only for the demolished part of a building where the owner prefers to use the unwanted part of the land; provided, however, that such preference shall be acceptable only where the condition of the partly demolished building conforms with the requirements of the appropriate city plan.

4. *Compensation for Fences*

The amount of compensation for a fence shall be determined by calculating the current cost per square meter or the unit cost required for constructing a similar fence.

5. *Compensation for Crops*

1) The amount of compensation for crops shall be calculated by multiplying the amount of yield that would have been collected from the land at maturity by the current market price of the crops.

2) the owner of ripe crops may, in lieu of compensation, harvest and collect the crops within the period fixed pursuant to Article 4 of the Proclamation.

6. *Compensation for Perennial Crops*

1) The amount of compensation for unripe perennial crops shall be determined by calculating the estimated cost for growing the plant.

2) The amount of compensation for ripe perennial crops shall be determined on the basis of the average annual yield, the current local market price of the crops and the cost of permanent improvement on land.

፯. <u>የዛፍ ካሣ አተማመን</u>

፩. የዛፍ ካሣ የሚሰላው በዛፉ የዕድገት ደረጃ ላይ ተመሥርቶ የወቅቱን የነጠላ ወይም የካሬ ሜትር ዋጋ በማውጣት ይሆናል።

፪. ባለንብረቱ በካሣ ክፍያ ፋንታ በአዋጁ አንቀጽ ፬ መሠረት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዛፉን ከመሬቱ ላይ አንስቶ መውሰድ ይችላል።

፰. <u>የጥብቅ ሣር ካሣ አተማመን</u>

፩. የጥብቅ ሣር ካሣ የሚሠላው የመሬቱን የሣር ምርታማነትና የሣሩን የወቅቱን የካሬ ሜትር የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

፪. ባለንብረቱ በካሣ ክፍያ ፋንታ በአዋጁ አንቀጽ ፬ መሠረት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሣሩን ከመሬቱ ላይ አንስቶ መውሰድ ይችላል።

፱. <u>በገጠር መሬት ላይ የተደረገ ቋሚ ማሻሻያ አተማመን</u>

በገጠር መሬት ላይ ለተደረገ ቋሚ ማሻሻያ ካሣ የሚተመነው ለምንጣሮ፣ ለድልደላና እርከን ለመስራት እንዲሁም ውኃ ለመከተርና ለሌሎች የግብርና መሠረተ ልማት የወጡትን የመሣሪያ፣ የጉልበትና የዕቃዎች የወቅቱ ዋጋ በማስላት ይሆናል።

፲. <u>ተዛውሮ የሚተከል ንብረት ካሣ አተማመን</u>

ተዛውሮ ለሚተከል ንብረት የሚከፈለው ካሣ ለንብረቱ ማንሻ፣ ማዛወሪያና መልሶ መትከያ የሚያስፈልጉ የባለሙያ፣ የማቴሪያልና የማጓጓዣ ወጭዎችን ግምት በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሠረት በማስላት ይሆናል።

፲፩. <u>ለማዕድን ባለፈቃድ ስለሚከፈል ካሣ አተማመን</u>

ለማዕድን ሥራ በማዕድን ባለፈቃድ የተያዘ መሬት በአዋጁ መሠረት የሚለቀቅ ሲሆን የሚከፈለው ካሣ አግባብ ባለው የማዕድን ህግ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል።

፲፪. <u>ለመካነ መቃብር ስለሚከፈል ካሣ</u>

፩. ለመካነ መቃብር የሚከፈለው ካሣ መካነ መቃብሩን ለማንሳት፣ ተለዋጭ ማረፊያ ቦታ ለማዘጋጀት፣ አጽሙን ለማዘዋወርና ለማሳረፍ እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለሚደረግ ሃይማኖታዊና በህላዊ ሥርዓት ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉትን ወጭዎች ያጠቃልላል።

7. *Compensation for Trees*

1 The amount of compensation for trees shall be determined on the basis of the level of growth of the trees and the current local price per square meter or per unit.

2) The owner of trees may, in lieu of compensation, cut and collect the trees within the period fixed pursuant to Article 4 of the Proclamation.

8. *Compensation for Protected Grass*

1) The amount of compensation for protected grass shall be determined on the basis of the productivity of the land and the current market price of the grass per square meter.
2) The owner of protected grass may, in lieu of compensation, cut and gather the grass within the period fixed pursuant to Article 4 of the Proclamation.

9. *Compensation for Permanent Improvement on Rural Land*

The amount of compensation for permanent improvement made on a rural land shall be determined by computing the machinery, material and labor costs incurred for clearing, leveling and terracing the land, including the costs of water reservoir and other agricultural infrastructure works.

10. *Compensation for Relocated Property*

The amount of compensation for a relocated property shall be determined by computing the estimated costs of labor, material and transport to be incurred at market value for removing, transferring and installing the property.

11. *compensation Payable to a Mining Licensee*

Where a mining site is expropriated pursuant to the provisions of the Proclamation, the compensation due to the licensee shall be determined by the relevant mining law.

12. *Compensation for Burial-ground*

1) The amount of compensation for a burial-ground shall be determined on the basis of the estimated costs to be incurred for removing the grave stones, preparing other burial-ground, transferring and relocating the corpse and for conducting religious and cultural ceremonies in relation thereto.

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት ወጪዎች የአካባቢውን የዕቃ፣ የትራንስፖርት አገልግሎትና የጉልበት የወቅቱን የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይሠላሉ።

፲፫. <u>የካሣ ስሌት ቀመር</u>

በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የሚከፈል የንብረት ካሣ መጠን የሚሰላበት ቀመር እንደሚከተለው ይሆናል፤

፩. የቤት ካሣ = የግንባታ ወጭ (በወቅቱ ዋጋ)
+ የመሬት ቋሚ ማሻሻያ ወጭ
+ የቀሪ ዘመን የመሬት ሊዝ ተመላሽ ክፍያ

፪. የሰብል ካሣ = የቦታው ስፋት (በካሬ ሜትር)
x የሰብል የገበያ ዋጋ በኪሎ ግራም
x በአንድ ካሬ ሜትር ስፋት ላይ የሚገኝ ምርት በኪሎ ግራም
+ የመሬት ቋሚ ማሻሻያ ወጭ

፫. ፍሬ መስጠት ያልጀመረ ቋሚ ተክል ካሣ = የተክል ብዛት (በእግር)
x በአንድ እግር የወጣ ወጭ ግምት
+ የመሬት ቋሚ ማሻሻያ ወጭ

፬. ፍሬ መስጠት የጀመረ ቋሚ ተክል ካሣ = ተክሉ በአንድ ዓመት የሚያስገኘው ምርት ብዛት (በኪሎ ግራም)
x የቋሚ ተክሉ ምርት የወቅቱ የገበያ ዋጋ
+ የመሬት ቋሚ ማሻሻያ ወጪ

፭. ተዛውሮ የሚተከል ንብረት ካሣ = የንብረቱ ማንሻ ወጭ
+ የማዛወሪያ ወጭ
+ የመልሶ መትከያ ወጭ

2. The amount of costs stipulated under Sub-Article (1) of this Article shall be determined on the basis of the current local market prices of materials, transport services and labor.

13. *Formula*

The formula for calculating the amount of compensation payable in accordance with the Proclamation and these Regulations shall be as follows:

1) Compensation for building = cost of construction (current value).
+ cost of permanent improvement on land
+ the amount of refundable money for the remaining term of lease contract

2) Compensation for crops = the total area of the land (in square meters)
x value of the crops per kilo gram
x the amount of crops to be obtained per square meter
+ cost of permanent improvement on land

3) Compensation for unripe Perennial Crops = number of plants (legs)
x cost incurred to grow an individual plant
+ cost of permanent improvement on land

4) Compensation for ripe Perennial Crops = the annual yield of the Perennial crops (in Kilo grams)
X the current price of the produce of the perennial crops
+ cost of permanent improvement on land

5) Compensation for relocated Property = cost of removal
+ cost of transferring
+ cost of reinstallation

፮. የጥብቅ ሣር ካሣ = ሣሩ የሸፈነው ቦታ በካሬ ሜትር
X የሚመረተው የሣር ምርት ወቅታዊ
የገበያ ዋጋ በካሬ ሜትር

## ክፍል ሦስት

## ምትክ ቦታና የመፈናቀያ ካሣ ስለመስጠት

፲፬. ለከተማ ቦታ ምትክ ስለመስጠት

ለህዝብ ጥቅም ሲባል ይዞታውን እንዲለቅ ለተደረገ የከተማ ነዋሪ የሚሰጠው ምትክ ቦታ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (፪) መሠረት ክልሎች በሚያወጡት መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

፲፭. ለገጠር መሬት ምትክ ስለመስጠት

ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሰብል፣ የጥብቅ ሣር ወይም የግጦሽ መሬት እንዲለቀቅ ሲደረግ ለተመሳሳይ አገልግሎት የሚውል ምትክ መሬት በተቻለ መጠን ይሰጣል።

፲፮. ለሰብልና ቋሚ ተክል መሬት ስለሚከፈል የመፈናቀያ ካሣ

፩. እንዲለቀቅ የተደረገ የሰብል ወይም የቋሚ ተክል መሬትን በተመለከተ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ መሠረት ምትክ መሬት የተሰጠ ከሆነ፣

ሀ) ከሰብሉ የሚገኘውን አማካይ ዓመታዊ ገቢ የሚያህል፣ ወይም

ለ) ከቋሚ ተክሉ የሚገኘውን አማካይ ዓመታዊ ገቢ ተክሉ የደረሰበት የዕድገት ደረጃ ለማድረስ በሚወስደው ዓመታት ቁጥር ተባዝቶ የሚገኘውን መጠን የሚያህል፣ የመፈናቀያ ካሣ ይከፈላል።

፪. እንዲለቀቅ የተደረገ የሰብል ወይም የቋሚ ተክል መሬትን በተመለከተ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ መሠረት ምትክ መሬት መስጠት ካልተቻለ የሚከፈለው የመፈናቀያ ካሣ ሰብሉ ወይም ተክሉ ያስገኘው አማካይ አመታዊ ገቢ በ፲ ተባዝቶ የሚገኘው መጠን ይሆናል።

፫. የሰብል ወይም የቋሚ ተክል አማካይ ዓመታዊ ገቢ የሚሰላው፣

ሀ) መሬቱ ከመለቀቁ በፊት በነበሩት አምስት አመታት በተገኘው ገቢ ላይ፣ ወይም

ለ) ሰብሉ ወይም ቋሚ ተክሉ ገቢ ያስገኘው ከአምስት አመት ላነሰ ጊዜ ከሆነ በነዚሁ አመታት በተገኘው ገቢ ላይ፣ ወይም



6) Compensation for protected grass = area covered by the grass per square meter
X the current market price of the grass per square meter

## *PART THREE*

## *PROVISION OF REPLACEMENT LAND AND PAYMENT OF DISPLACEMENT COMPENSATION*

14. *Provision of Replacement Urban Land*

The provision of replacement land to an urban dweller whose landholding has been expropriated for public purpose shall be governed by directives issued by Regional States in accordance with Article 14 (2) of the Proclamation.

15. *Provision of Replacement Rural Land*

Where land used for growing crops or a protected grass or pastoral land is expropriated for public purpose, the possessor of such land shall, as much as possible, be provided with a plot of land capable of serving a similar purpose.

16. *Displacement Compensation for Land Used for Crops and Perennial Crops*

1) Where a replacement land has been provided in accordance with Article 15 of these Regulations with respect to expropriated land used for crops or perennial crops, displacement compensation equivalent to the following amounts, shall be paid:

(a) the price of the annual average yield of crops obtained from the land; or

(b) the price of the annual average yield of perennial crops multiplied by the number of years required to attain the level of growth of the perennial crops.

2) the amount of displacement compensation payable with respect to land used for growing crops or perennial crops shall, where it is impossible to provide replacement land in accordance with Article 15 of these Regulations, be ten times the price of the average yield of crops or perennial crops obtained from the land.

3. The average annual yield of crops or perennial crops shall be calculated on the basis of:

a) the yield obtained from the land for the last five years; or

b) where the land was used for les than five years, the yield obtained for the actual years the land was used; or

ሐ) ሰብሉ ወይም ተክሉ ዓመታዊ ገቢ መስጠት ያልጀመረ ከሆነ በአካባቢው ባለው ተመሳሳይ የይዞታ መጠን ከተመሳሳይ ሰብል ወይም ቋሚ ተክል በአምስት ዓመታት በሚገኝ ገቢ ላይ፣ ተመሥርቶ ይሆናል።

፲፯. ለጥብቅ ሣር ወይም የግጦሽ መሬት ስለሚከፈል የመፈናቀያ ካሣ

፩. እንዲለቀቅ የተደረገ የጥብቅ ሳር ወይም የግጦሽ መሬትን በተመለከተ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ መሠረት ምትክ መሬት የተሰጠ ከሆነ፣ ከጥብቅ ሣሩ ወይም የግጦሽ መሬቱ የተገኘውን አማካይ አመታዊ ገቢ የሚያህል የመፈናቀያ ካሣ ይከፈላል።

፪. እንዲለቀቅ የተደረገ የጥብቅ ሳር ወይም የግጦሽ መሬትን በተመለከተ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ መሠረት ምትክ መሬት መስጠት ካልተቻለ የሚከፈለው የመፈናቀያ ካሣ ጥብቅ ሣሩ ወይም የግጦሽ መሬቱ ያስገኘው አማካይ አመታዊ ገቢ በ፲ ተባዝቶ የሚገኘው መጠን ይሆናል።

፫. የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ ፫ ድንጋጌዎች የጥብቅ ሣር ወይም የግጦሽ መሬት አማካይ አመታዊ ገቢን ለማስላት በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፲፰. ለተወሰነ ጊዜ ለሚለቀቅ የገጠር መሬት ስለሚከፈል የመፈናቀያ ካሣ

የገጠር መሬት እንዲለቀቅ የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ከሆነ የመፈናቀያ ካሣው ስሌት ማባዣ መሬቱ እስኪመለስ ድረስ ያሉት ዓመታት ቁጥር ይሆናል። ሆኖም በዚህ መንገድ ተሰልቶ የሚገኘው ካሣ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ ወይም ፲፯ መሠረት ከሚከፈለው መጠን መብለጥ የለበትም።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፱. ካሣ የማይከፈልባቸው ንብረቶች

በአዋጁ መሠረት መሬቱ የሚለቀቅ ስለመሆኑ የተሰጠው ውሣኔ ለባለይዞታው ከደረሰ በኋላ ለተሠራ ወይም ለተሻሻለ ቤት፣ ለተዘራ ሰብል፣ ለተተከለ ቋሚ ተክል ወይም በመሬት ላይ ለተደረገ ቋሚ ማሻሻያ ካሣ አይከፈልም።

c) where the crops or perennial crops have not yet started giving annual yield, the yield of similar crops or perennial crops obtained from a similar area of land in the locality for the last five years.

17. *Displacement Compensation for Protected Grass or Grazing Land*

1) where a replacement land is provided in accordance with Article 15 of these regulations with respect to expropriated protected grass or grazing land, displacement compensation equivalent to the annual average income obtained from the land shall be paid.
2) The amount of displacement compensation payable with respect to the protected grass or grazing land shall, where it is impossible to provide replacement land in accordance with Article 15 of these Regulations, be ten times the annual average income obtained from the land.
3) The provisions of Sub-Article (3) of Article 16 of these Regulations shall, mutatis mutandis, be applicable with respect to calculating the average annual income derived from a protected grass or grazing land.

18. *Displacement Compensation for Provisional Expropriation of Rural Land*

Where a rural land is expropriated only for a limited period of time, the multiplication factor for calculating the displacement compensation shall be the number of years for which the land is cleared; provided, however, that the compensation obtained by such calculation shall not exceed the amount payable under Article 16 or 17 of these regulations

*PART FOUR*

*MISCELLANEOUS PROVISIONS*

19. *Properties for which Compensation is not Payable*

There shall be no payment of compensation with respect to any construction or improvement of a building, any crops sown, perennial crops planted or any permanent improvement on land, where such activity is done after the possessor of the land is served with the expropriation order.

፳. መረጃ ስለመስጠት

፩. ኮሚቴው በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ንብረት ለመተመን አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች አግባብ ካላቸው የፌዴራል፣ የክልል ወይም ሌሎች አካላት መጠየቅ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጥያቄ የቀረበለት አካል የተጠየቁትን መረጃዎች ወዲያውኑ ለኮሚቴው መስጠት አለበት፡፡

፫. በተጠየቁት አካላት ዘንድ መረጃዎቹ አለመኖራቸው ሲረጋገጥ ኮሚቴው የአካባቢውን የንብረቱን ዋጋ ቅኝታዊ ጥናት ራሱ ያካሂዳል፡፡

፳፩. የንብረት ዝርዝር ስለመያዝ

ለአዋጁና ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር እንዲለቀቅ በሚወሰን መሬት ላይ የሚገኙትን ንብረቶች በሚመለከት መረጃ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

፳፪. ባለይዞታነትንና ባለንብረትነትን ስለማረጋገጥ

በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ካሣ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ሰው የሚለቀቀው መሬት ሕጋዊ ባለይዞታና ካሣ የሚከፈልበት ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

፳፫. ስለግምት ሥራ ወጭዎች

፩. አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት ለኮሚቴው አባላት የሚከፈል አበልን ጨምሮ በዚህ ደንብ መሠረት ንብረት ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎችን የወረዳና የከተማ አስተዳደሮች ይሸፍናሉ፡፡

፪. መሬት የሚለቀቀው በአስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ጥያቄ መሠረት ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ወጭ በሚመለከተው አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ይሸፈናል፡፡

፳፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯/፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

20. *furnishing of Data*

1) The committee shall request the relevant federal, regional or other bodies to furnish any data necessary for determining the value of a property in accordance with the Proclamation and these Regulations.

2) Any body requested under Sub-Article (1) of this Article shall hand over the data immediately to the Committee.

3) where the data is not available with the requested bodies, the committee shall conduct its own survey on the local market price of the property.

21. *Records of Property*

A woreda or a city administration shall, for the purpose of the implementation of the Proclamation and these Regulations, record properties situated on a landholding subjected to an expropriation order.

22. *Evidence of Possession and Ownership*

Any person who claims for payment of compensation in accordance with the Proclamation and these Regulations shall produce proof of legitimate possession of the expropriated landholding and ownership of the property entitling compensation.

23. *Valuation Costs*

1) Woreda and city administrations shall cover the costs of valuation of properties in accordance with these regulations, including payment of per diem to members of the Committee in accordance with the relevant laws.

2) The costs referred to Sub-Article (1) of this Article shall be covered by the concerned implementing agency where the expropriation is made upon its request.

24. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 4th day of July 2007

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC*

*REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ